ርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን
Re'ese Adbarat Debre Selam Kidest Mariam
The Ethiopian Orthodox Tewahido Religion Church
1350 Buchanan St., N.W., Washington, D.C. 20011 Tel.: (202) 726 4115 Fax: (202) 726 4056

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## ዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ዛሬ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዞታ በነበረው በደሴ ከተማ ሣር አምባ በቅድስት አርሴማ ስም ቤተ ክርስቲያን ሢሠሩ በነበሩት ላይ በታጠቁ የመንግሥት ወታደሮች ለተገደሉት የዘመናችን ሰማዕታት የፍትሐትና የምህላ ጸሎት በተደረሰበት ወቅት የሰማዕታቱን ግድያ አስመልክቶ ዋሽንግተን ዲሲ ከሚገኘው የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የወጣ መግለጫ::

በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ማህፀን ምድር ተፀንሰህ ተወልደህ ጡቶቿን እየጠባህ ተስማሚ አየሯን እየተነፈስክ እንጀራዋን እየተመገብክ በተራራ ሽንተረሯ እየቦረቅህ የአደክ በውጭ የአለህ ኢትዮጵያዊ ወገኔ በፖለቲካ አመለካከትህ የተነሳ ሳትወድ በግድ ውብ ሀገርህን አስደሳች ሁሮህን ትተህ የኮበለልክ ጊዜ ጎድሎብህ ሆድ ብሶህ የምጣኔ ሀብት ጥገኛ በመሆን በውጭው ዓለም በየሀገሩ የተበተንክ ሁሉ ዛሬ ብትናገር ትሰማለህ ብትቸር ትመግባለህ ታለብሳለህ ወገንህን ለመርዳት ከአንተ የተሻለና የቀረበ ማን አለ! ባዕድ ቢረዳ ኢትዮጵያዊነት ወኔን ሰልቦ ፖለቲካዊ መብቶችን አሳጥቶ ብሉይና ሐዲስ የተስማሙላት ጥንታዊት ተዋሕዶ እምነቱን አስለውጦ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው::

በሁሉም ዘርፍ የአንተን እድል ያላገኘው በሀገር ቤት የአለው ወገንህ በዘር ፖለቲካ የተነሳ ነፃነቱ ተገፎ ፍትሕ አጥቶ እንዳይናገር አንደበቱ ታፍኖ እንዳይጽፍ እጁ ታሥሮ ከአንዱ እስቴት ወደ ሌላው እስቴት እንዳይዘዋወር ሥራ እንዳይሠራ በዘር በክልል እግር ብረት ተቀፍድዶ ሲሰቃይ ዘመናትን እያስቆጠረ ነው:: እንደልቡ የሚሰበሰብበት አምልኮቱን የሚፈጽምበት እርስ በርሱ ተገናኝቶ ሃሳቡን የሚለዋወጥበት ዐይን ለዐይን የሚተያይበት የነበረው አንድ ቦታ ያውም አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምባቸው አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ:: ያም በዛ ተብሎ ለዘመናት ተከባብሮና ተስማምቶ ይኖር የነበረውን ኅብረተ ሰብ ሙስሊሙ በክርስቲያኑ ክርስቲያኑ በሙስሊሙ ላይ እንዲነሳ፤ ክርስቲያኑን በሙስሊሙ ተበድሏል ሙስሊሙም በክርስቲያኑ ስቃይ አድርሶበታል በማለት አንዱን በአንዱ ላይ በማስነሳት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የዩዲትና የግራኝ መሐመድ ጊዜ እየተደገመ የሚገኝበት ዘመን ይመስላል::

## በውጭ ዓለም ለምትኖረው ወገኔ

እግዚአብሔር አምላክህ ከአውሬ መንጋጋ አላቆ ስንት ውጣ ውረዱን አሳልፎ በውጭው ዓለም በሀብት አክብሮ በልጆች ጎብኝቶ አክብሮ የአኖረህ ለዓላማ ነው:: የዮሴፍ ወደ ግብፅ መሰደድ ወገኖቹን ከረኀብ ለመታደግና በአንድነት ለማሰባሰብ፡ የሙሴ በግብፅ መወለድ ወገኖቹን ከ400 ዓመታት በኋላ ከፈርኦን የባርነት አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የእግዚአብሔር ዓላማ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጠዋል:: በዘመነ ሐዲስም በድጋሚ በመጀመሪያው ምዕት ዓመት በጥጦስ ስደት የደረሰባቸው እስራኤላውያን ከ1878 ዓመታት ስደት በኋላ ተመልሰዋል:: ዛሬ ሀገራቸውና ሕዝባቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማስረጃ አያስፈልገውም ሁላችንም የዐይን ምስክሮች ነንና::

የዚህ ዓይነቱ ነፃነት እንዲሁ የመጣ አልነበረም:: በነበሩበትና በተሰደዱበት አህጉራት ሁሉ እንደዛሬው መገናኛዎች በአልነበሩበት ወቅት የቦታ ርቀትና ሳያገድባቸው ሁሉም አንድ ኃሣብ ነበራቸው ለዚህ ሁሉ የረዳቸው በጽዮን ስም ማኅበር አቋቁመው

ባህላቸውን፣ እምነታቸውን፣ቋንቋቸውን ሳይቀር ጠብቀው አንድነታቸውን አስተባብረው በአደረጉት የትግል መስዋዕትነት ነው:: ዛሬ አንተም በውጭ የአለህ ወገኔ የዚህ ዓይነት ጉዞ ያስፈልግሃል:: ለልጅህ ታሪክህን ንገረው ሃይማኖትህን አስተምረው ባህልህን አስረክበው ሙሴ ወገኑን ነፃ የአወጣው ሁሉንም ከእናቱ ስለተረከበ ነው:: አንተም የእኔ ነው የምትለውን ሁሉ አስረክበው እውነትን እንዲናገር እውነትን እንዲከተል አበክረህ አስጨብጠው:: ከውሸት ተላቀህ አላቀው በውሸት የከበረ በውሸት ነፃነቱን የተጎናፀፈ የለምና:: ሀገር ቤት ለአለው ወገንህ በሁሉም ዘርፍ የምታደርገው የአልተቆጠበ እርዳታ የሚደነቅ ነው:: በዚያው ግፋበት ከእግዚአብሔር በታች የአለኸው አንተ ነህና::

## <u>በሀገር ቤት ለአለህ ክርስቲያን ወገኔ</u>

ይህ የአለህበት ጊዜ በግልጽ «አብያተ ጣኦታት ይትረኃዋ አብያተ ክርስቲያናት ይተአጸዋ» ተብሎ በአዋጅ ባይነገርም በዘመነ ዲዮቅልጢያኖስ በዘመነ ሰማዕታት በዘመነ ጉዲትና በዘመነ ግራኝ መሐመድ ይፈጸም የነበረው እየተፈጸመብህ ነው:: ደስ ይበልህ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጅተሀልና::

በአሰቦት ገዳም አካባቢ የነበርክ «መኑ የሀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ ምንዳቤኑ ተሰዶኑ ረሃብኑ ዕርቃንኑ መጥባህትኑ ጻዕርኑ»ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል መከራ ወይስ ጭንቀት ወይሰ ስደት ወይስ ራብ ወይስ እራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይሰ ሰይፍ ነውን? የአለውን ተገንዝበህ ዐይንህ እያየ ገደል የተጣልከው ማንም ደራሽ የአልነበረህ የት ወደቅህ የአልተባልክ የአራዊት መኖ የሆንክ ወገኔ ደስ ይበልህ::

በጂማ በሸሻ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የጻድቁን በዓል ለማክበር ከተለያየ ቦታ መጥታችሁ በአገልግሎት ላይ የነበራችሁ ካህናት ቀሲስ ከፍ ያለው ይግለጡና ቀሲስ ጌትነት ወልዱ እንዲሁም ሥጋውን ደሙን ለመቀበል በዓሉን ለማክበር የነበራችሁ ምዕመናንና ምዕመናት ወ/ሮ ዓለምነሽ ደበላ፣ወ/ሮ ምሕረት ረዳ፣አቶ ተፈራ ተኮላና አቶ አቦየ በየነ በዚህ ሰዓት እናስባችኋለን:: አንገታችሁ በቆንጨራ ተቀላ አስከሬናችሁ በእሳት ጋየ ደስ ይበላችሁ ጌታችሁንና አምላካችሁን በግብር ስለመሰላችሁት «ወዘሰ ደልአ ለነፍሱ በዝንቱ ዓለም የዐቅባ ለሕይወት ዘለዓለም»ሲተረጎም ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል ነፍሱን በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘለዓለም ሕይወት ይጠብቃታል» ዮሐ.12፤25፣ሉቃ.17፤33 የተባለው ተፈጽሞላችኋልና:: የስንዴ ቅንጣት ብዙ ፍሬ የምታፈራው ስትሞት እንደሆነ ጌታችን የተናገረው ተግባራዊ ስለሆነላችሁ አሁንም ደስ ይበላችሁ:: ስማችሁ በሰማያዊው መዝገብ ተጽፏልና እንዲሁም የ21ኛው ምዕት ዓመት ሰማዕታት በመሆን በሩን ስለከፈታችሁልን የ21ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ሰማዕታት እያልን እናከብራችኋለን::

በተመሰሳይ መልኩ በአለፈው ሳምንት በደሴ ከተማ በሣር አምባ አካባቢ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ በነበረው ስፍራ ላይ በቅድስት አርሴማ ስም ካህናትን ከየቦታው በማሰባሰብ መቃኞ(ድንኳን) በመቀለስ መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሰጠበት ሲሆን የበለጠ አገልግሎቱን ለማስፋትና ለማጠናከር ቤተ ክርስቲያን ሰርታችሁ ለማስመረቅ ደፋ ቀና በምትሉበት ወቅት የአለአሰባችሁትና የአልገመታችሁት በማንም ህሊና የማይገመት የማይታሰብና ተደርጎ የማይታወቅ ዱብ ዕዳ በመንግሥት ወታደር በጥይት ሕይወታችሁን አጣችሁ የሰማዕትነትን ክብር ተቀበላችሁ:: በድርጊቱ ብናዝንም የሰማዕትነት ክብር ስለተቀበላችሁ ደስ ይበላችሁ እንላለን:: በመግቢያችን ላይ ዘመነ ዲዮቅልጢያኖስን ያነሳነው ለዚህ ነው:: የታሰራችሁ በቁም እስር የምትጠበቁ ከእያላችሁበት እየታደናችሁ የምትታሰሩ ዛቻ ማስፈራራት የደረሰባችሁ እንዳላችሁ ተረድተናል:: ይህ ለክርስትናው መስፋፋትና መጠናከር የበለጠ ኃይል ነው:: ሚስማር ሲመታ የበለጠ እንደማያጠነክረው የታወቀ ነውና:: «ማስፈራራታቸውን አትፍሩ» ተብሏልና ባላችሁበት በሃይማኖታችሁ ጽኑ በምግባራችሁ ጠንክሩ እኛም በፀሎታችን እንዘክራችኋለን በሀሳባችንም እንደግፋችኋለን::

## በከፍተኛ ማዕረግ ላይ ለምትገኙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች

«ወይእዜኒ ዕቀቡ ርዕሰክሙ ወኩሎሙ መራዕየ ዘሎቱ ሤመክሙ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳተ ከመ ትርዐዩ ቤተ ክርስቲየኑ ለእግዚአብሔር እንተ አጥረያ በደሙ» ሲተረጎም«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» የሐዋ.ሥራ 20፥28 ቃሉ እንደሚለው መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ እንደሚሰይም ነው:: በመንፈስ ቅዱስ የተሰየመ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መሥራት እንዳለበት ግድ ነው:: ማንም ተሿሚ የሿሚውን ፈቃድ መፈጸምና ማስፈጸም ግዴታ አለበት:: የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ፈቃድ ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም፣ትዕግሥት፣ርህራሄ፣ቸርነት፣ገርነት፣ንጽህናና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው:: ገላ.5፥22፣ኤፌ.5፥4

አባቶቼ የመንፈስ ቅዱስ ምሬት ይህንንና የመሳሰለውን ያካትታል:: ይህ ሕይወት በማንኛ ችንም ሕይወት ውስጥ ይነበባል? ተግባራዊ ሲሆን ይታያልን? ሹመቱ ከመንፈስ ቅዱስ አይደለምን? ቅዱሳት መጻሕፍት ይዋሻሉን? ጥያቄውን ለተጠያቂው ክፍል እተወዋለሁ::

በውስጥም በውጭም ያላችሁ ቅዱሳን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ሁላችንም ጥያቄ ላይ ወድቀናል:: መልስ መፈለግ አለብን:: መልሱን ካላገኘን ከበን የምንበጠብጣት ቤተ ክርስቲያን አትኖርም የምናስከትላቸው ምዕመናን አይኖሩም:: እነርሱም ከሌሉ እኛም አንኖርም:: ህልውናችን ሚዛኑን ደፍቷል:: ህልውና ከሌላ ምንም የለምና:: የተሰጠንን ጥያቄ ያልሆነ ምክንያት በመስጠት እራሳችንን ከማታለል እንቆጠብ:: ወደ ህሊናችን እንመለስ:: ቅዱሳት መጻሕፍትን እንመርምር::

«ሥራህን አውቃለሁ ስምህ ህያው እንደሆነ አንተ ሙት እንደሆንህ እንግዲህ ተመለስ ባትመለስ ግን እንደሌባ ድንገት እደርስብሀለሁ በማንኛውም ሰዓት እንደምመጣ አታውቅምና::» ራዕይ 3፥2-3

## በመንግሥታዊ ሥልጣን ላይ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን

የማንኛውም ሀገር መንግሥት እንደ መንግሥትነቱ ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎችንና ሰብአዊ መብቶችን

- ሀ. የማክበር Obligation to respect
- ለ. የመጠበቅ Obligation to protect
- ሐ. የመፈጸም Obligation to fulfill

ግዴታ አለበት:: የኢትዮጵያ መንግሥት የዓለም አቀፉን መርሆ መጣስ ብቻ ሳይሆን በአ ወጣው ህገ መንግሥት የተደነገገውን ሰብዊ መብቶችን በመጣስ የፈጸመቸውና የሚፈጽማቸው በግልጥ በዓለም ዙርያ እርቃነ ሥጋውን እንዲቆም አድርገውታል ::

በ1997 ዓ.ም በምርጫው ዙርያ በርካታ የንፁሐን ደም መፍሰስ እንዲሁም በአሪሲ በጅማና በኤሉባቡር የተፈጸመው ጭፍጨፋ የንብረቶች መውደም ይህ ነው አይባልም:: ዛሬም ቢሆን በየጊዜው በዜጎች ላይ የሚፈጸመው ኢ ሰብአዊ ተግባር በተለይ በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ የሚሰቃዩ ብዙ ናቸው::

በአለፈው ሳምንት በደሴ ከተማ በሣር አንባ በቅድስት አርሴማ ስም የአምልኮት ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን በመሥራታቸው ብቻ መብታቸውን በመጠበቅና በማስጠበቅ ፈንታ በንጹሐንና ሰላማውያን ዜጎች ላይ በመንግሥት ወታደሮች በጥይት ተደብድበው ሕይወታቸውን የአጡ የዘመናችን ሰማዕታት ምሥክሮች ናቸው::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን አማንያን ላይ ይህን የመሰለ በማን አለብኝ ስሜት ተነሳስቶ አስቃቂ ድርጊት ሲፈጸም ይህ የመጀመርያው አይደለም:: ስለሆነም ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ ለምነቱና ለቤተ ክርስቲያኑ ዘብ መቆም አለበት::

የዚህ ዓይነቱ አፈጻጸም የእርስ በርስ ግጭትን የሰላም መናጋትን የሚያስከትል በመሆኑ መንግስት በቸልታ መመልከት የለበትም። በመንግሥት ስም ወንወጀል የሚፈጽሙ ከአሉ መንግሥት ተከታትሎ መያዝና አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው አበክረን እንጠይቃለን።የተፈጸመውን አረመኔያዊ የግድያ ድርጊት እናወግዛለን የዚህ ዓይነቱ ጨፍጨፋና እንግልት እንዳይደገም አጥበቀን እናሳስባለን።የሰላም ኀይሎች የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች በዓለም ዙርያ የአሉ ክርስቲያኖች ትኩረት እንዲሰጡበት በድጋሜ እናሳስባለን።

«ወስብሐት ለእግዚአብሔር»

**ሃምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም**
**07/08/09**